

የሥራ



ሰነ መለኮት

ዘላለም መንግሥቱ

የሥራ ስነ መለኮት

አንድ፤ መግቢያ

ሁለት፤ ፕሮቴስታንታዊ የሥራ ስነ ምግባር

ሦስት፤ ለሥራ ተፈጥረናል

አራት፤ ድንኳን ሰፊ አገልጋይ

አምስት፤ ጉቦ፥ ቁማርና ሐሰተኛ ነቢያት (ሀ፥ ጉቦ)

ስድስት፤ ጉቦ፥ ቁማርና ሐሰተኛ ነቢያት (ለ፥ ቁማር)

ሰባት፤ጉቦ፥ ቁማርና ሐሰተኛ ነቢያት (ሐ፥ ሐሰተኛ ነቢያት)

ስምንት፤ ሥራና ዕረፍት

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል አንድ፤

መግቢያ

‘ሥራ ክቡር ነው!’ በሶሻሊስት ኢትዮጵያ ዘመን ብዙ የተነገረ ቃልና መርህ። በሶሻሊዝም ፍልስፍና ሥራ ክቡር ብቻ ሳይሆን የፈጣሪ ያህል ሚናም ተቀዳጅቶአል። ‘ሰውን ሰው ያደረገው ሥራ ነው።’ የአገራችን ዘፋኝ የዘፈነው ሐረግ ነው፤ ምንጩ ግን እርሱ አይደለም። ምንጩ እንዲያውም ሰውን የፈጠረው ሥራ ነው (Labour created man himself.) የሚል ነው።

“Labour, is the primary basic condition for all human existence, and this to such an extent that, in a sense, we have to say that labour created man himself . . . Thus the hand is not only the organ of labour, *it is also the product of labour.* ” (C. Marx and F. Engels).[1] ማርክስ እና ኤንግልስ የጻፉትን ሥራዎች Marxian Thought በተባለው የፍልስፍና ኮርስ በዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት ስማር የሰማሁት ቃል ነው። ይህ አሳብ ሰው በአዝጋሚ ለውጥ ከዝንጀሮ ወደ ሰው እንዲለወጥ ሥራ የተጫወተውን ሚና ለመግለጥ ከተሰጠ ትንተና የተወሰደ ነው።

ሰው ከዝንጀሮ አልመጣም፤ ሥራም ሰውን አልፈጠረም። የዛሬዎቹ ዝንጀሮዎችም ወደ ሰውነት እያዘገሙ አይደሉም። የዳርዊን ፍልስፍኖት ሃይማኖትን እና መጽሐፍ ቅዱስን በመጻረር ሂደት የራቀ ሆኖ ለዘመኑና ለኋለኞችም ሳይንሳውያን የፈጣሪን ሕልውና የማስካድ የአማራጭ ያስጨበጠ ትምህርተ ክህደት ነው።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ፍጡር ነው። ሰውን የፈጠረው ሥራ ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ነው። እርሱም ሰውን የፈጠረው በራሱ በሥራ ነው። እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። (ዘፍ. 2፥7) ‘አበጀው’ የሚለው ቃል፥ (יִיצֶר) ያጻር יָצַר ከሚለው የመነጨ) ሠራው፥ ቀረጸው፥ ልክ ሸክላ ሠሪ እንደሚሠራው አደረገው ማለት ነው። ሁሉ ነገር በቃል ተፈጥሮ፥ ሰው ግን፥ ‘ሁን’ በሚል ቃል ሳይሆን በሥራ ነው የተፈጠረው። እግዚአብሔር ሠራተኛ እግዚአብሔር ነው።

[1] Karl Marx and Frederick Engels, *Selected Works*, Vol . II, Foreign Languages Publishing House, Moscow, 1951. P. 2.

የሥራ ስነ መለኮት

ሰው ከተፈጠረ በኋላስ? ሰው ከተፈጠረ በኋላ ራሱም ሠራተኛ ተደርጎ ነው በተፈጠረባት ስፍራ እንዲኖር የተደረገው፤ እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው። ዘፍ. 2፥15። ማበጀትና መጠበቅ ሥራ ነው። ገና ከጠዋቱ፥ ገና ከፍጥረት ጀምሮ ነው ሰውና ሥራ የተቆራኙት።

እግዚአብሔር ሠራተኛ ከሆነ፥ እኛም እግዚአብሔርን ልንመስል ከተሠራንና ከተጠራን እኛም ሠራተኞች ልንሆን ይገባናል።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል ሁለት፤

ፕሮቴስታንታዊ የሥራ ስነ ምግባር

በምዕራቡ ዓለም የታወቀና ብዙ የተባለለት የሥራ ሐረግ፥ The Protestant Work Ethic (የፕሮቴስታንት የሥራ ስነ ምግባር) የተባለው ነው። ዛሬ ዛሬ እየመነመነ ብቻ ሳይሆን እየቀረም የመጣ ይመስላል። ፕሮቴስታንቶች ታታሪ፥ ትጉህ እና ታማኝ ሠራተኞች ናቸው። ፕሮቴስታንቶች የቃሉ ተማሪዎችም ናቸው። ቃሉ ለሥራ የሚተጉ፥ የማይቦዝኑ፥ የማይለግሙ፥ ሐኬተኞች ያልሆኑ እንዲሆኑ ያስተምራል። ቃሉ ስለ ሥራ የሚያስተምረውን ያነበቡና ያንን ለመኖርና ለመተግበር የሚጥሩ ናቸው።

መጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ ስለ ትጋት ብዙ ተጽፎአል። የታካች እጅ ችግረኛ ታደርጋለች፤ የትጉ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች። ምሳ. 10፥4። ይህን የመሰሉ ብዙ ጥቅሶች ይገኛሉ። ቃሉም ለጌቶች ስለ መገዛት ሲያስተምር፥ ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ። 1ጴጥ. 2፥18። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ። ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤ ኤፌ. 6፥6-7። ይህ ለክርስቲያን ሎሌዎችና ባሪያዎች የተነገረ ቢሆንም ዛሬ በሥራ ገበታ የምንገኝ ሁላችንንም የሚመለከት ነው። ይህ የፕሮቴስታንት የሥራ ስነ ምግባር ነው።

የሥራ ስነ መለኮት

በተቃራኒው በአገራችን በኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት በመንፈሳዊነት ስም እና በባህላችንም ከኩራትና ንቀት ጋር የሥራ ባህል ሲበደል ኖሮአል። ሃይማኖታዊውን ብንመለከት በወር ውስጥ ላሉት 30 ቀናት 44 ታቦታት ሲደመር ተደልድለዋል። የሕዝባችን አብላጫ ሕዝብ አርሶ አደርና በኦርቶዶክሳዊነቱም አጥባቂም ባይሆን ቀናዒ ነው። እንደየ ታቦታቱ ስርጭት በንቃትና በትጋት ከሚሠራባቸው ይልቅ የማይሠራባቸው ቀናት ይበዛሉ። እንደ ታላቅ ወንድማችን የምናየው አባታችን ያሳደገው ገበሬ አበበ በዓላቱ ሲበዙና አባቴም፥ 'ዛሬ ማርያም ናት፤ ከነገ ወዲያ ጊዮርጊስ ነው፤ . . .' እያለ ሥራ ሲከለክለው፥ አቤ ቢቸግረው ቀን ቀን የሸመናም የእንጨት መጥረብ ሥራም አንዳንዴ አረቂም እየጠጣ ይውልና ማታ ማታ በሬዎች ጠምዶ በጨረቃ ያርስ የነበረበትን ጊዜ አስታውሳለሁ።

አርቶዶክሳዊው ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ባህላችንም አስናፊና ሙያን ናቂ ነው።ቁርበት ፋቂ፥ መጫኛ ነካሽ፥ ቁጢት በጣሽ፥ ስር ማሽ፥ ሸክላ ሠሪ፥ ብረት ቀጥቃጭ፥ ወዘተ፥ በማለት ባለ ሙያዎችን አዋራጅ ባህል አለን። እነዚህ ባለ ሙያዎች የሚያመርቱትን ምርት አለመጠቀም ደግሞ የማይቻል ነው። አገራችን ለዘመናት ከደሸየችው በታች ብትሆንም አያስገርምም። ለአገራችን ድህነት ሃይማኖታዊውም ባህላዊውም ኩራትና ሙያ ናቂነት፥ ሥራ ጠይነትና ሥራ አስፈቺነት የተጫወቱት ሚና መኖሩን የምንክድ አይመስለኝም። ይህ በአጠቃላይና በጅምላ ሲታይ እንጂ እጅግ ታታሪና ሠራተኛ የሆኑ ሠራተኞችና ወገኖች መኖራቸውንም በእርግጥ አንክድም። ያውም ባልተመቻቸ ሁኔታ ኑሮን አሸንፈው ለሌሎች የተረፉም አሉን።

ፕሮቴስታንታዊው የሥራ ስነ ምግባር የምዕራቡ ሥልጣኔ ሞተርና አስቀጣይ ነው። ሥራ አይናቅም፤ በትጋት ይስሠራል፤ በልፋት የተገኘ ጥሪት ደግሞ ዋጋው ይታወቃልና ጥበቃና ክብካቤ ይደረግለታል። ስለዚህ በምዕራቡ ዓለም የቆንቋናነት ሳይሆን የቁጠባ ባህል ዳበረ፤ Frugality ይሉታል። ገንዘብን እንደተቀበሉት ጸጋ አድርገው በጥንቃቄ ማስተዳደርን ልማድ አደረጉት፤ Christian Capitalism ይሉታል። ልጆችም ከልጅነታቸው ጀምሮ ሥራን እንደ ግዴታ ሳይሆን እንደ ደስታና መኖሪያ እንዲለማመዱት ወላጆች ተጨማሪ ሥራ እያሠሩ የኪስ ገንዘብ በመስጠት ያበረታቷቸዋል። ሲያድጉና ሲጎለምሱም ይህ ከልጅነት የሠረጸ ባህል ትቷቸው አይሄድም።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል ሦስት፤

ለሥራ ተፈጥረናል

ለሰው ከሚበላና ከሚጠጣ በድካሙም ደስ ከሚለው በቀር የሚሻለው ነገር የለም፤ ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር እጅ እንደ ተሰጠ አየሁ። መክ. 2፥24

ባለፈው ክፍል ስለ ፕሮቴስታንታዊ የሥራ ስነ ምግባር ስናይ ሥራ ክቡር መሆኑ ተገልጦአል። የምዕራቡን ዓለም የሥራን ዋጋ የሚያሳየን ሌላ ነጥብ ከፍያው በሥራ መጠን ወይም በሰዓት መሆኑ ነው። የማይለዋወጥ ወርሃዊ ክፍያ የሚከፈላቸው ቢኖሩም እነዚህ የተወሰኑና የታወቀና የተለካ ሥራ የሚሠሩ ናቸው። ከዚያ በተረፈ፥ እንኳን ቀንና ቀናት ሰዓቶች መቀነስም የሥራ ጊዜ ቅናሽ በመሆኑ የክፍያ ቅናሽ ያስከትላል።

ሥራ የተፈጠረው ሰው በተፈጠረ ቀን ነው። ሰው ሲፈጠር የተሰጠው ተግባር ከአምላኩ ጋር ኅብረት ከማድረግ ሌላ ዔድን ገነትን ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ ነው። በመጀመሪያ ይህ ሥራ አስደሳችና አርኪ ትጋት እንጂ ብዙ ልፋት፥ ጥረትና ድካም ያልነበረበት ተግባር ነበረ። ሆኖም ሥራ በመጀመሪያም የነበረና በረከት ሆኖ የተሰጠ ስጦታ ነው። ሥራ ድካም የሆነው፥ በጥረትና ግረት እንጀራን በፊት ወዝ ሙበላት የተጀመረው ከውድቀት በኋላ ነው። የሌላውን ድካም በግድ፥ በማታለል፥ በመስረቅ መውሰድ የተጀመረውም ከውድቀት በኋላ ነው።

ይህ የሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት በአይሁድ ዘንድ ጠልቆ የገባ ጉዳይ ነው። አይሁድ ታታሪ ሠራተኞች ናቸው። እያንዳንዱ ቤተ ሰብ መተዳደሪያ ሙያ አለው። ለምሳሌ ጥቂት ብናይ፥ ቦኤዝ እና ኤልሳዕ ገበሬዎች፥ አሞጽ ወርካ ለቃሚና ላም ጠባቂ፥ ዘኬዎስና ማቴዎስ (ወይም ሌዊ) ቀራጮች፥ ስምዖን ቀኮርበት ፋቂ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ዓሣ አጥማጆች፥ ሉቃስ ባለ መድኃኒት፥ ጳውሎስና እነ አቂላ ድንኳን ሰፊዎች፥ ጌታ ራሱ አናጺ ወይም ጸራቢ ነበሩ። ግንበኞች፥ አንጥረኞች፥ ልብስ አጣቢ፥ ቀማሚዎች፥ ጸሐፊዎች፥ ወታደሮች፥ መርከበኞች፥ ወዘተ፥ ብዙ ሙያዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፈዋል።

ሙያ ተወድዶ የሚሠሩት ተግባር ነው። መሥራት መቻል በራሱ ደስታን የሚፈጥር ነገር ነው። ስጦታ ነው። እግዚአብሔር ጉልበትን፥ አእምሮን፥ ችሎታን፥ ዝንባሌን፥ ክህሎትን፥ ፍላጎትን ሲሰጠን እንድንሠራ ነው። እርሱ ሠሪ ነውና እኛም ሠሪዎች እንድንሆን ነው። እርሱን እንድንመስል ነው። እርሱ እንደፈጠረ እኛም እንድንፈጥር ነው፤ ልዩነቱ እርሱ የፈጠረው ከዐልቦ ሲሆን እኛ የምንፈጥረው እርሱ ከፈጠረው ወስደን ነው።

የሥራ ስነ መለኮት

ፈጠራችን ዋጋ ፈጣሪ ነው። ለምሳሌ፥ አንድ ኪሎ ጥጥ 50 ብር ቢያወጣ፥ ተፈትሎ ክር ቢሆን 100 ብር ያወጣል፤ ቢሸመን 200 ብር ቢሆን ተሰፍቶ ሸሚዝ ቢደረግ 400 ብር ሊያወጣ ይችላል። ሥራ፥ ማለትም፥ ጉልበት፥ ጊዜ፥ ጥበብ በጥሬ ነገር ላይ ዋጋ ይጨምራሉ፤ ምርቱን ክቡር ያደርጋሉ።

ይህን የሥራ ስነ መለኮት ስንጀምር በማርክሳዊ የሥራ ምንነት ነበር የጀመርነው። በማርክሳዊ ኢኮኖሚ የዋጋ ወይም ተመን ቀመር፥ c+L=W ነው። c (constant capital ጥሬ ዕቃ) ሲደመር L (labor ሥራ) ይሁናል W (worth ዋጋ ወይም ክቡርነት)። ሠራተኞች ስንሆን ዋጋ ወይም ክቡርነት ፈጣሪዎች መሆናችን ነው።

እግዚአብሔር ሥራ ሲሰጠን መባረኪያችንን እና መብባረኪያችንን ነው የሰጠን። ሥራ ራሱ በረከት ነው፤ ሥራ የራሳችን መሠሪያችንና መቀረጫችን ነው። በዚህች ምድር በሥጋ ሕይወት የምንኖረው ለተወሰነ ጊዜ ነው። ሥራ ሌሎችን መባረኪያ ወይም መጥቀሚያ ከሆነ፥ ይህን ማድረግ የምንችለው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው ማለት ነው። ይህ ራሱ እድል ነው። መሥራት እየፈለጉ ያልቻሉና የማይችሉ ሰዎች እንዳሉ ማወቅ ይህን የመሥራት እድል እንድናደንቅ ያደርገናል።

መሥራት እየፈለጉ አለመቻል ብቻ ሳይሆን እየቻሉ አለመፈለግም አለ።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል አራት፤

ድንኳን ሰፊ አገልጋይ

ያለፈው ክፍል፥ መሥራት በረከት ወይም መታደል መሆኑንና መሥራት እየፈለጉ አለመቻል ብቻ ሳይሆን እየቻሉ አለመፈለግም መኖሩን በሚጠቁም አሳብ ነበር ያለቀው። መሥራት በረከት ከሆነ መሥራት እየቻሉ መሥራት አለመፈለግ የበረከት ተቃራኒ የሆነው መርገም ነው። እንደዚህ ያሉ ሰዎች ዳተኞች፥ ሐኬተኞች፥ ሰነፎች፥ ሸክሞች ናቸው። ይህ ስንፍና ደግሞ ወደ አፍራሽነት ይወስዳቸዋል። አውደልዳዮችና በሰው ጉዳይ ጣልቃ ገቦች ይሆናሉ። አጭበርባሪና አምታችም ይሆናሉ። በቀላሉ ገንዘብ ማግኛ ይመስላቸውና፥ ደግሞም ይሆንላቸውና 'አገልጋዮች' የሚሆኑም አሉ። አገልጋይ መሳዮች ማለት ነው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን፥ ሌዋውያን፥ በተለይም አሮናውያን (ካህናት) የመቅደስ አገልጋዮች ናቸውና ከ12ቱ ነገዶች ጋር ተቆጥረው ርስት አልተቀበሉም። የቀሩት ነገዶች ከየርስታቸው መንደሮችና መሰምርያዎች (የከብት ማሰማርያ) ሰጥተዋቸው በየነገዱ ተበትነው ይኖሩ ነበር። ለመኖሪያም ከየነገዱ የሚቀበሉት ኣሥራት፥ በኩራትና የፈቃድ ስጦታ ቀለባቸው ነበረ። መሰምርያዎች ነበሯቸው ማለት መጠነኛ እርሻና ከብት ማርባትን ያከናውኑ የነበረ ይመስላል። በተለይ ካህናቱ የመቅደሱ ቋሚ አገልግሎት የእነርሱ ነውና በሌላ ተግባር ያልተጠመዱ ነበሩ።

በአዲስ ኪዳን፥ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፥ ዛሬም ጭምር፥ እንደ ካህናት ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የሚያገለግሉ ወይም እንዲያገለግሉ የተጠሩ አሉ። እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔርና ከሚያገለግሉት ማኅበር ጥሪ፥ የሚያገለግሉበት መስክ ጸጋ፥ የአገልግሎቱ ሸክምና አደራ፥ ማገልገያው ስጦታና ትምህርት ያላቸው ሰዎች ከሆኑና ሙሉ ግዜያቸውን ሰጥተው እንዲያገለግሉ የሚያግዟቸው ተቀባይ ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም ወጌል ወዳልደረሰበት ስፍራ ሄደው የሚያገለግሉ ከሆኑ ላኪ ወገኖች ከኖሩ እየታገዙ ሊያገለግሉ የተገባ ነው። መጽሐፍ፡- የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር፥ ደግሞ፡- ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ይላልና። 1ጢሞ. 5፥15።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች (ጥሪ፥ ጸጋ፥ ሸክም፥ አደራ፥ ስጦታ፥ ትምህርት) ሳይኖሩአቸው አገልጋይ የሚባሉም አሉ። ሌላ ነገር መሥራት ስላልቻሉ፥ መሥራት የሚያስችል የሙያ ትምህርት ወይም ስልጠና መውሰድ ስላልቻሉ ወይም ስላልፈለጉ፥ ሐኬተኞች፥ ዳተኞችና ሰነፎች ስለሆኑ፥ ሌሎች ሙያዎችን ሞክረው ሳይሆንላቸው ቀርቶ ይህኛውን እንደ አማራጭ ስለወሰዱ፥ ጡረታ ከወጡ በኋላ ጥሪ አለኝ ስላሉ፥ አገልግሎት ሥልጣንና ከሥልጣን ጋር የተቋጠሩ ጥቅማ ጥቅሞች ስላሉበት፥ አምታችና አጭበርባሪ የሆኑቱ በሐሰት ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ የሚቻልበት፥ ብዙ በቀላሉ አማኞች የሆኑ ተታላዮች ወይም ተላላዎች የሚገኙበት መስክ በመሆኑ፥ ወዘተ፥ ወዘተ፥ 'አገልጋይ' የሆኑ ወይም የተባሉ ናቸው።

የሥራ ስነ መለኮት

ከእነዚህ ብዘዎቹ እግዚአብሔርም ቤተ ክርስቲያንም ያልጠሯቸው ራሳቸውን በራሳቸው የሾሙ ሹመኞች ናቸው። ሽክም ያላቸው ሳይሆኑ ራሳቸው ሥራ ጠል የማኅበር ሸክሞች ናቸው። እነዚህ እረኞች ሳይሆኑ ምንደኞች ናቸው። መጋቢዎች ሳይሆኑ ተመጋቢዎች፥ ሠራተኞች ሳይሆኑ ሞያተኞች (ዮሐ. 10፥12-13) ናቸው።

ባለፈው ክፍል አይሁድ ሁሉ የእጅ ሙያ ያላቸው ሠራተኞች መሆናቸውን ተመልክተናል። ጳውሎስ ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ ያገለገለ አገልጋይ ሳለ፥ ግን የእጅ ሙያው ድንኳን መስፋት ነበረና ድንኳን እየሰፋ ያገለገለ አገልጋይ ነው፤ ሐዋ. 18፥2-3። በቆሮንቶስ እንዲህ አገለገለ። ለኤፌሶን አማኞችም የመጨረሻ የአደራ ቃል ሲተውላቸው፥ እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ። አላቸው፤ ሐዋ. 20፥34። ለተሰሎንቄ ሰዎችም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን። አላቸው፤ 1ተሰ. 2፥9።

ዛሬም፥ ‘ድንኳን ሰፊ አገልጋይ’ (tent making minister) የሚባለው የተለመደ ቃል ከዚህ ከጳውሎስ አገልግሎት የተወሰደ ቃል ነው። ከላይ ያልኩት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት ጥሪ፥ ሽክም፥ ጸጋ፥ ትምህርት፥ ወዘተ፥ እነደተጠበቀ ሆኖ ዛሬ ብዙ አገልጋዮች ይህንን መሆን ቢችሉ እንዴት ትልቅ ለውጥና ለዋጭ አገልግሎት በኖረን የነበረ ይመስለኛል።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል አምስት፤

ጉቦ፥ ቁማር፥ እና ሐሰተኛ ነቢያት (ሀ፥ ጉቦ)

ሥራ ብዙ ጠላቶች፥ ብዙ አምካኞች አሉት። ዜጎች መንግሥታቸውን ይመስላሉ ይባላል። በከፊል እውነት ነው። ሌባ መንግሥት ሌባ ዜጋ፥ ታታሪ መንግሥት ታታሪ ዜጋ፥ አጭበርባሪ መንግሥት አጭበርባሪ ዜጋ ይፈጥራል። ባለ ሥልጣኖች መሪን፥ የበታች አለቆች የበላይን፥ መደዴው ሕዝብም እነርሱን ይመስላል። ያለ ጉቦ ምንም መሥራት የማይቻልባቸው አገሮች አሉ፤ አገራችን አንዷ ናት። ጸረ ሙስና እየተባለ ኮሚሽኖች ቢመሠረቱም ስር የሰደደ ዛፍን መቁረጥ እንጂ መንቀል አይቻልም። ሲቆረጥ ደግሞ ከብዙ ቅርንጫፎች ጋር እንደገና ይበቅላል።

በአገራችን አሁን ምንም ነገር ያለ ጉቦ መሥራት የማይቻል ሆኗል። ጥቅም ለማግኘት ከነሳ ማንነት ቀጥሎ ወይም እኩል ትልቁ መሣሪያ ጉቦ ነው። ከወረፋ እስከ ፈተና ውጤት፥ እስከ ዲግሪና ዲፕሎማ፥ ከሥራ ቅጥር እስከ ሹመትና እድገት፥ እስከ ግብር ቅነሳ እስከ ቀረጥ ስረዛ፥ እስከ ርስትና ይዞታ፥ ወዘተ ያለ ዋጋ፥ ያለ ሥራ በጉቦ ማግኘት ተችሎአል። ጉቦ የሠሩትን ወንጀል መቀነሻ ብቻ ሳይሆን ያልሠሩትን ዋጋ ማግኛም ነው። ጉቦ ሥራን በአቋራጭ አልፎ ከሠሪዎች እኩልና እንዲያውም በላጭ ሆኖ መገኘት ነው።

በምኖርበት በምዕራቡ ዓለም ነገሮች በአግባቡ የሚሠራበት መስመር የተዘረጋ ስለሆነ ጉቦ አይታወቅም ማለት ይቻላል። ለምሳሌ የትራፊክ ሕግ ጥሰህ ፖሊስ ቢያቆምህ የሚጠይቅህ መታወቂያህንና ኢንሹራንስህን ብቻ ነው። ይሁንና በዚህ በምዕራቡ ዓለምም እንኳ አበሾችም (ሌሎችም አሉበት) ይህን ከፉ የሥራ አምካኝ ባህል እያስተዋወቁና እያስለመዱ ይገኛሉ። በቅርብ በሄድኩባቸው ሁለት ግዛቶች በሁለት የተለያዩ የሥራ መስኮች ኢትዮጵያውያን ከተሰማሩባቸው በኋላ ሕጉ እንዴት እየታጠፈና እየተጣሰና ጉቦ እንዴት የተለመደ መሆኑን ስሰማ አዘንኩ። ይህ ሳይሠሩና ሳይለፉ፥ ሳይሰለጥኑና ሳይማሩ፥ በአግባቡ ሳይሆን በአቋራጭ ለመበልጸግ የሚደረግ ከፉ ነገር ነው፤ ሥራ ጠልነት ነው።

ጉቦ መስጠትን ራሱን ሥራ ነው የሚል ትውልድ ተወልዶልናል። ሥራ የማይሉት የሥራ ማስኬጃማ ማሳለጫ ነው ይሉታል። ጉቦ የሥራ ጠላት ነው። የሚሠራውና ሕጋዊው እየተዘለለና እየታለፈ፥ እየተሰረዘና እየተረገጠ መሆኑ መረሳት የለበትም። በስደተኞች ካምፕ እንኳ የሌላውን ወረፋ ጉቦ ከፍለው፥ ፎቶ አስነቅለውና የራሳቸውን አስለጥፈው የራሳቸው ባልሆነ ስምና ታሪክ ወደ ምዕራቡ ዓለም መጥተው የሚኖሩ አሉ። የስሞቹ ባለቤቶች ከስፍራቸው መነቀላቸውን አያውቁም። ጉቦ የግብር (የሥራ) ብቻ ሳይሆን የግብረ ገብነትም ጠላት ነው።

ስለ ጉቦ ብዙ ማለት እንችላለን፤ በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን።



የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል ስድስት፤

ጉቦ፥ ቁማር፥ እና ሐሰተኛ ነቢያት (ለ፥ ቁማር)

ሌላው የሥራ አምካኝ ቁማር ነው። ቁማር ሳይሠሩ ለመበልጸግ እድልን ተስፋ ማድረግ ነው። እድል ያለ የሚመስል ግን የማይጨበጥና የሌሎች ቁማርተኞችን ገንዘብ የመውሰድ ሂደት ነው። ቁማር ያልሠሩትንና ያልለፉበትን የመውሰድ፥ ያልዘሩትን የማጨድ ተግባር ነው። ‘ትንሽ ዘርቶ ብዙ ማጨድ ነው፤’ የሚሉ አይጠፉም። ቁማር መዝራት ሳይሆን መበተን ነው። ማጨድ ሳይሆን መሰብሰብ ከሆነም ሌሎች የበተኑትን መሰብሰብ ነው። ቁማርተኞች ሲያገኙ መታደል፥ ሲያጡ አለመታደል ነው ብለው ያምናሉ። ቋንቋቸው፥ ‘ቀናኝ፥ ታደልኩ’ ወይም፥ ‘አልቀናኝም፥ አልታደልኩም’ ነው። እድል የምትባል ግዑዝ ምናባዊ አምላክ በማሰብ ወይም ባለማሰብ ያመልካሉ።

ቁማርተኛ ተቀምጦ ከሆነ ቦታ ተበልቶ ዱብ የሚል እድልን ያምናል፤ ሎተሪን ያምናል፤ እግዚአብሔርን አያምንም፤ ቃሉንም አይታዘዝም። ቁማርተኛ ሥራን አይወድድም። ሥራ ከትንሽ ጀምሮ የሚያድግ፥ ገንዘብ፥ ጉልበትና ጊዜ የሚፈስስበት ዋጋ የሚጠይቅ ሂደት ነው። ቁማርና ሎተሪ ግን በትንሽ ቆምሮ ሌሎች የበተኑትን በብዙ የሚያሳፍስ ነው፤ ግን ብዙ ሚሊዮኖች የበተኑትን አንድና ሁለቱ ብቻ ናቸው የሚያፍሱት። የቁማር ቀመሩ ይኸው ነው። ብዙዎቹ ሚሊዮኖች እንዲያው በትነዋል ማለት ነው።

ቁማር የሥራ አምካኝና የታታሪነት ገዳይ ነው። ይህንን ጉዳይ ክርስቲያንና እንትን በተሰኘ መጽሐፌ፥ ክርስቲያንና ቁማር በሚል እዑስ ርእስ እና በYouTube ክርስቲያንና ቁማር በሚል ርእስ በሦስት ክፍል አካፍያለሁ፤ ከክፍል አንድ ጀምሮ ማየት ለሚፈልጉ ክፍል አንድ እዚህ ይገኛል፤ https://www.youtube.com/watch?v=RhZvywBrQLo

የሥራ ስነ መለኮት

ባለፈው ክፍል ያየነው ጉቦ እና ይህኛው ቁማር ሁለቱም የሥራ አምካኞች ናቸው። ከነዚህ ጋር መጠቀስ ያለበት ሦስተኛው ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት ናቸው። የብልጽግና ወንጌል የሚሉት እኩይ ትምህርት አላቸው። የብልጽግና ወንጌል በውስጡ ወንጌልም ብልጽግናም የለበትም። ወንጌል ቅጥያ ካለበት ያ ወንጌል ሌላ ወንጌል ነው።

ቁማርና ጉቦን በአንድነት ከሐሰተኛ ነቢያት ጋር ያጣመርኩበት ምክንያት አለኝ። ጉቦን ያያያዝኩበት ምክንያት ነሆነንና ተላላ (የተታለሉ) ሰዎች፥ 'የእግዚአብሔር ሰዎች' የሚሏቸው ሐሳውያን እንዲጸልዩላቸውና ቃል እንዲያወጡላቸው ብለው የሚሰጡት ገብዘብ ስለሆነ ነው። ይህ የሚሰጧቸው ገንዘብ በሌላ ቃል ጉቦ ክርስትና ተነሥቶ ማለት ነው። ከቁማር ጋር ያያያዝኩት ደግሞ፥ ለሐሰተኞቹ ነቢያትና ሐዋርያት የሚሰጡት ገንዘብ ሳይሠሩና ሳይለፉ ለማግኘትና ለመበልጸግ ብለው የሚሰጡት በመሆኑ ነው። በመሆኑ ነው። የቁማርን ቀመር አውቀውትም ይሁን ሳያውቁት የሚቆምሩ ሰነፎች ናቸው። ቆማሪዎቹም አስቆማሪዎቹም ሥራ ጠሎች ናቸው።

የሚቆምሩበትን ገንዘብ 'አሸንፈው' የሚበሉት ሰባኪዎቹ መሆናቸውን አያውቁም። 'የብልጽግና ወንጌል' እየሰበኩ በእነርሱ 'አገልግሎት' ላይ ዘር እንዲዘሩና መዋዕለ ንዋይ እንዲያፈስሱ ያበረታቷቸዋል፤ ያደፋፍሯቸዋል። እነዚያም ቁጭ ብለው ያልሰሩትን ከሰማይ የሚወርድ መና ይጠብቃሉ። 'ያልዘራኸውን ታጭዳለህ!' ሲሏቸው፥ ላንቃቸው እስኪሰነጠቅ፥ 'አሜ . . . . ን!' ይላሉ። ሰነፎች! የሥራ ጠላቶች! መዝራት ዋጋ ይጠይቃላ! መዝራት ለፍቶ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግን ይጠይቃላ! ያዕ. 5፥ 7። እግዚአብሔር የእጆቻችንን ሥራ ይባርካል እንጂ የሌሎችን ልፋት ባርኮ አይሰጠንም፤ ዘዳ. 28 በሙሉና በተለይ ቁ፣ 12። እርሱ ሰውን ሲፈጥርም ለሥራና ለተግባር ነው የፈጠረው። ሰው ከወደቀ በኋላ ሥራ ልፋትን ጠየቀ እንጂ፥ መልኩ ተቀየረ እንጂ ሥራ አልቀረም።

ሐሰተኛ ነቢያትና ሐዋርያት የገንዘብ ናፋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ የምትሐት ገንዘብ ናፋቂዎችና አስናፋቂዎች ናቸው።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል ሰባት፤

ጉቦ፥ ቁማር፥ እና ሐሰተኛ ነቢያት (ሐ፥ ሐሰተኛ ነቢያት)

ሐሰተኛ ነቢያትና ሐዋርያት የሥራ አስናፊዎች ብቻ ሳይሆኑ የገንዘብ ናፋቂዎች ብቻ ሳይሆኑ የምትሐት ገንዘብ ናፋቂዎችና አስናፋቂዎች ናቸው። ከእነርሱ የተነሣ የወንጌላዊ ክርስትና መልክና ስም የነደፈና የተሰደበ ሆኖአል። ከአምስት ዓመታት በፊት ሐሰተኛ ነቢይ እስራኤል ዳንሳ ወደ ከተማችን መጥቶ በነበረ ጊዜ ከረጫቸው የውሸት ትንቢቶች አንዱ ለአንድ ወንድም የ18 አውሮፕላን ባለቤት እንደሚሆን ነበር። እነዚህ ሰዎች ቁጥር ሲጠሩ ምንም ሒሳብ የሚያውቁ አይመስሉም። ዳንሳማ አካውንቲንግ የተማረና ባንክ የሠራም አይመስልም።

ይህንን የሥራ ስነ መለኮት ስንጀምር ፕሮቴስታንታዊ የሥራ ስነ ምግባር ጉዳይ ተወስቶ ነበር። በአገራችን ወንጌላዊ ክርስትና ገብቶ ስር ከያዘ ከና ወደ 100 ዓመቱ ነው። እስከ ጥቂት (20ና 30 ዓመት) ዓመታት በፊት ድረስ ወንጌላውያ አማኞች፥ ስማቸውን ያለ ምክንያት የሚያቆሽሹ ጠፍተው ባያውቁም፥ የሚታወቁበት መታወቂያ ታማኝነት፥ ታታሪ ሠራተኝነት፥ ተማሪነት ወይም አካዳሚያዊ ልቀት፥ ሰላማዊነትና ቅድስና ነው። በርኩሰትና በቅሌት፥ በሌብነትና በውሸት፥ በዳተኝነትና ልግምተኝነት፥ በጣልቃ ገብነትና ጠበኝነት ታምተውም ተከስሰውም አያውቁም። ቢከሰሱ በእምነታቸው ብቻ ነበር።

ዛሬ፥ በተለይም ነቢያትና ሐዋርያት ነን የሚሉ ሰዎች እንደ አሸን ከፈሉባቸው ካለፉት 10ና 15 ዓመታት ወዲህ ግን ነገሩ ተቀይሯል። ሥራ ጠላቱዎች የሆኑ አምታቾችና አጭበርባሪዎች፥ ሳይሠሩ ሊበለጽጉ፥ ሳይገዙ ሊሸጡ፥ ሳይለፉ ሊከብሩ፥ ሳይዘሩ ሊያጭዱ የሚፈልጉና እንዲፈልጉ የሚያነሣሱ በዙ፥ ተባዙም። የሐሰተኞች ዋና ግባቸው ገንዘብና ገንዘብ ብቻ ነው። ተከታዮቻቸውም ሥራ የለሽ ገንዘብ ናፋቂዎች ሆኑ።

ከ20ና 25 ዓመታት በፊት ይህ የሥራ ጠልነት የብልጽግና ወንጌል ትምህርት ወደ አገራችን ከገባ በኋላ፥ 'ይህ መኪና የኔ! ያ ቤት የኔ! ይህ ሕንጻ የኔ፥ ያቺ ልጅ የኔ!' እያሉ ለራስ መውሰድ (claim ማድረግ ይሉታል ያው ከእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች የተወረሰ ኑፋቄ ስለሆነ) የጊዜው ፋሽን ሆኖ ነበር። ነገሮቹና ቁሳቁሶቹ ላይ እጅ መጫንም ተጀምሮ ነበር። ጉልበት ያላቸውና የተማሩም እንኳ ሆነው፥ ሥራ ትተው መቦዘን ጀመሩ። አንዱ ይህንን የስሕተት ትምህርት በሞቅታ ይሰብክና ያስደርግ የነበረ ሰባኪ ሳምንታዊ ስብሰባዎቹ ላይ መባሲዞር እየጎደለ፥ እያነሰ መጥቶ ባዶ መሆን ሲጀምር ደነገጠና፥ 'ልጆች፥ ወንድሞች፥ ውጡና ሥራ ሥሩ። ጫማ መጥረግም ቢሆን ሥሩ፤ አንድ ቀን የጫማ ፋብሪካ ባለ ቤት ትሆናላችሁ። ሽኖራ መሸጥም ቢሆን ሥሩ፤ አንድ ቀን የስኳር ፋብሪካ ባለ ቤት ትሆናላችሁ።' ማለት ጀመረ። ይህንን ማለት የነበረበት ቀድሞ ቢሆን እንዴት ጥሩ ነበር።

የሥራ ስነ መለኮት

ነቢያትና ሐዋርያት ነን ባዮች የምትሐት ገንዘብ ወደ ተከታዮቻቸው ኪስና ቦርሳና አካውንት እንደሚገባ ሲተነብዩ ይህ እንደማይሆን በእርግጥ እያወቁት በገንዘብ ፈላጊዎች ልቡና እየተጫወቱ ነው። እነዚህ ሰዎች ድራማ የሚሠሩ ሰዎችን አሰናድተው ነው የሚጫወቱት። በድብቅ ኪስና ቦርሳ ውስጥ ቀስ ብለው የሚጨምሩ ሰዎች አሏቸው። ከኮርኒስ የወርቅ ብናኝ ያበነኑ አሉ፤ ወርቅ ሳይሆን ወርቅ የሚመስል የፕላስቲክ ብናኝ ነው እንጂ! ይህንን ከአገራችን የሞከሩ የሉም፤ ከአፍሪቃ ቡሺሪ፥ ከደቡብ አሜሪካ ማልዶናዶ ሞክረዋል።

ጨዋታው በተለይ የማልዶናዶ በጣራ አየር ማስገቢያ (vent) ውስጥ እና ማርገብገቢያ (fan) በኩል በሚያበንኑ ሰዎች መሆኑ ተጋልጧል። አካውንታቸው ውስጥ ብር የገባላቸው ሰዎችም አሉ፤ የዋሆቹ ከሰማይ የወረደ የመና አካውንት አድርገው ተቀብለውታል። ነገር ግን ወርቁ በአሜሪካ ወደ American Geological Survey ላብራቷር ተወስዶ ሲፈተሽ ወርቅ እንዳልነበረው ሁሉ የኛዎቹም ብሩን ወደ ብሔራዊ ባንክ ቢወስዱ ያልተፈጠረ መሆኑን ያውቁ ነበር። ወደ አካውንታቸው የገባው ከየትኛው አካውንት መሆኑን ቢጠይቁና ቢያስመረምሩም ያውቁ ነበር። ግን ማሰቢያ ከተወሰደና ስንፍና አናት ላይ ከወጣ ያለ ሥራ የሚገኝ ሎተሪያዊ ገንዘብ ተበልቶ አይጠገብም።

ለሐሰተኞቹ ነቢያትና ሐዋርያት ነን ባዮች የሰው ኪስና ቦርሳ ወይም አካውንት ውስጥ ገንዘብ ማስገባት ኪሳራ አይደለም ታዲያ? ኪሳራ አይደለም፤ ትንሽ ሰጥቶ ከብዙዎች መሰብሰቢያ ብልሃት ነው። ሳይዘሩ የሚያጭዱትን አስልተው ነው የዘሩ የሚመስሉት። ይህ እንደሆነ ያዩና የሰሙ ስግብግቦች በገፍ መጥተው ይከተሏቸዋል፤ ይሰጧቸዋል፤ ይበዘበዛሉ። ነቢያትና ሐዋርያት ነን ባዮቹ በአጭር ጊዜ ይከብራሉ። ሐሳውያኑ የሚያጭዱት ሌሎች የዘሩትን መሆኑን አንርሳ።

ሥራ ተባርኮ የተሰጠን ትእዛዝና ኃላፊነት መሆኑን እንደገና እናስታውስ። ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ሐዋርያት ግን የቃሉ ተጻራሪ የሆኑ ሥራ ጠልና የሥራ አስጣይ ማስነፊያና ማደንዘዣ መርፌዎች ናቸው።

የሥራ ስነ መለኮት - ክፍል ስምንት (የመጨረሻ)፤ ሥራና ዕረፍት

እግዚአብሔር የፍጥረቱን ቁንጮ ሰውን ከፈጠረ በኋላ ዐረፈ። እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። ዘፍ. 2፥2።

እግዚአብሔር ያረፈው ደክሞት አይደለም። መፍጠርም እርሱን ጉልበት አልጠየቀውም። ዐረፈ የሚለው አሳብ የሥራውን ወይም የፍጥረት ተግባሩን መፈጸሙን፥ ፍጥረት ተሠርቶ መጠናቀቁን አመልካች ቃል ነው። ከዚያ በኋላ የሚፈጠር ነገር አዲስ ነገር የለም፤ ቆመ፤ አበቃ ማለት ነው። የዕብራይስጡ ቃል שָׁבַת (ሻባት) ወይም እኛ ሰንበት የምንለው ማለት ነው። ሰንበት የቀኑ ስም የሆነው የዕረፍት ቀን ስለሆነ ነው።

ኋላ በሕጉ ውስጥ ስድስት ቀን እንዲሠሩና በሰባተኛው ቀን እንዲያርፉ ተደጋግሞ ተነገራቸው፤ የሥራ ከብቶችም፥ ባሪያዎችም ሳይቀር እንዲያርፉ ሕግ ሆነ፤ ዘጸ. 16፥26፤ 20፥9-11፤ 23፥12፤ 31፥15-17፤ ዘሌ. 23፥3፤ ዘዳ. 5፥13።

ሰባተኛው ቀን ቀኑ ቅዳሜ ነው? ወይስ እሁድ የሚለው ነጥብ አከራካሪ አይደለም። ነጥቡ የቀኑ የትኛነት ሳይሆን የሥራና የዕረፍትን ሚዛን የመጠበቅ ጉዳይ ነው። ዐረብ አገር የሚኖሩ ክርስቲያኖች እሁድ የሥራ ቀን ስለሆነ ሰንበታቸው ዐርብ ነው። በአንዳንድ ኩባንያዎች የየሰዎች የሥራ ቀናትና ፈረቃዎች ይለያያሉና አንዳንዶች ብዙዎቹ የሚያርፉበት የዕረፍት ቀን የሥራ ቀናቸው ሊሆን ይችላል። በራሳቸው የዕረፍት ቀን ያርፋሉ ወይ? ነው ጥያቄው።

አንዳንድ ሰዎች ሥራ ላይ ሳይሆን ዕረፍት ላይ ያተኩራሉ። ሕይወትን የሚለኩት በዕረፍታቸውና በተዝናኖታቸው ነው። ከሥራ ይልቅ የሚያርፉበት ቀን ደስታ ይሰጣቸዋልና የሚሠሩበት አንሶ፥ የሚያርፉበት እንዲበዛ ይመኛሉ፤ ይጥራሉም። ሥራን እንደ መከራ ይቆጥራሉ። ሌሎች ደግሞ ሥራ፥ ሥራ፥ ሥራ፥ ሥራ እያሉ ከአንዱ ፈረቃ አንድ ሥራ ወደ ሌላው እየተሯሯጡ በቀን 16 ሰዓትና ከዚያም በላይ እየሠሩ፥ በሳምንት ሰባቱንም ቀን እየሠሩ፥ ገንዘብ፥ ገንዘብ፥ ገንዘብ፥ ገንዘብ እያሉ የምሚዋትቱ ሰዎች ናቸው። በመክ. 4፥8 አንድ ሰው ብቻውን አለ፥ ሁለተኛም የለውም፤ ልጅም ሆነ ወንድም የለውም፤ ለድካሙ ግን መጨረሻ የለውም፥ ዓይኖቹም ከባለጠግነት አይጠግቡም። ለማን እደክማለሁ፥ ሰውነቴንስ መልካሙን ነገር ለምን እነፍጋታለሁ? ይላል። ይህም ደግሞ ከንቱ ነገር ክፉም ጥረት ነው። ተብሎ እንደተጻፈው ነው።

የሥራ ስነ መለኮት

እነዚህ በአንድ በኩል ያሉት ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ሥራ ፈትና ቦዘኔ የሆኑ ታካች ሰዎች አሉ። ጳውሎስ፥ ደግሞ ከእናንተ ጋር ፡-ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና። እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን ለመሥራት አትታክቱ። እንዳለው የመሰሉ ደግሞ አሉ። 2ተሰ. 3፥10-13።

ለክርስቲያን የሥራ ባህል እጅግ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል የዕረፍት ጊዜም ተፈላጊ ነው። የዕረፍት ቀን አንዱ ግቡ በሥራ ተጠምዶ የሰነበተ አካልን ማሳረፍ ብቻ ሳይሆን፥ በተግባር ምክንያት ስትባክን የሰነበተችን ነፍም የመመገብ ቀን ነው። ሁሉም ቀን፥ የሥራ ቀንን እና ሥራን ራሱንም ጨምሮ የአምልኮም ቀንና የአምልኮ መገለጫ መስክ ቢሆኑም ሰባተኛ ቀን የተለየ የአምልኮ ቀንም ነው።

ሥራና ዕረፍት ለሰው ሁሉ፥ ለክርስቲያንም ሚዛናዊነቱ ተጠብቆ መሄድ አለበት።

ተጠናቀቀ።